## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

**ስለ አራቱ መንፈሳዊ ሕጎች ሰምተሃል?**

1) እግዚአብሔር ስለሚያፈቅርህ ለሕወትህ አሰደናቂ እቅድ ሰጥቶሃል?

> "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" ዮሐንስ 3፡16

2) ሰው ኃጢአተኛ የሆነ ባህርይ ስላለውና በዚህም ምክንያት ከእግዚአብሔር ስለ ተለየ እግዚአብሔር ለእርሱ ያለውን ፍቅርና እቅድ ሊለማመድ አይችልም።

> "ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል።" ሮሜ 3፡23

3) ኢየሱስ ክርስቶስ ለኛ በመሞቱ በእርሱ በኩል ብቻ ሰው ወደ እግዚአብሔር ይደርሳል።

> "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" ዮሐንስ 14፡6

4) ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛችንና ጌታችን አድርገን በመቀበል እግዚአብሔር አምላክ ለኛ ያለውን ፍቅርና እቅድ ልናውቅና ልንለማመድ እንችላለን።

> "ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።" ዮሐንስ 1፡12



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የእርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።" (ሮሜ 5፡8)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**April 29, 2018** | **ሚያዚያ 21፤ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | እህት ሰናይት ከበደ |
| አምልኮ....................... | ዘማሪ ተመስገን ማርቆስ |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ሰለሞን ወመኅ |
| ቃል ............. | ነብይ መድኅን ገብረሥላሴ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" (ዮሐ. 3፡16)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| **መሪ** | **ቀን** | **አድራሻ** |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመኅ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### የእግዚአብሔር ፍቅር።

ፍቅር ጥልቅ ነገር ነው። ብዙ ጊዜ አንረዳውም ነገር ግን እንለማመደዋለን። ፍቅር አያስገድድም ነገር ግን ብርቱ ገፊ ነው። ከያኒያን ዜማን ከግጥም አዋህደው፤ ቀለም በቡርሽ አጣቅሰው፤ ድርሰት ከምናብ አፍልቀውና ምስል ከድምጽ አቀናብረው ስለ ፍቅር ጥልቀት፣ ጥንካሬና ውበት ይቀኛሉ። መጽሐፍ ቅዱስም የፍቅርን ኃይል ሲገልጽ "ፍቅር እንደ ሞት የበረታች ናትና ... ብዙ ውኃ ፍቅርን ያጠፋት ዘንድ አይችልም" ይላል። (መኃ 8፡ 6-7) እግዚአብሔርም ሰውን የወደደበት ፍቅር እጅግ ብርቱና ጥልቅ ነው። እግዚአብሔር አንድ ልጁን ለመስቀል ሞት አሳልፎ እስኪሰጥ ድረስ ሰውን ሁሉ ወዷል። እግዚአብሔር እኛ በሕይወት እንኖር ዘንድ ሃጢያት የማያውቀውን አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ስለኛ በደል በመስቀል እንዲደቅና እንዲሞት በመፍቀድ ለእኛ ያለውን ወሰን የሌለውን ፍቅሩን አሳይቷል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል የሞተው በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የለየውን የኃጢያት ግድግዳ በሞቱ አፍርሶ ለሚያምን ሁሉ የሚሆን የደህንነትን መንገድ ለማበጀት ነው። እግዚአብሔር ሰውን በምሳሌው ፈጥሮ እንዲበዛና ምድርን እንዲሞላት፣ ምድርንም እንዲገዛና እንዲያስተዳድር ባርኮት፣ ከእርሱም ጋር ሕብረትን እያደረገ በገነት እንዲኖር በክብር ስፍራ አስቀምጦት ነበር። ነገር ግን ሰው በዲያቢሎስ ተንኮል ተታሎ የፈጣሪውን ትዕዛዝ በመተላለፍ መንፈሳዊ ሞትን ሞተ። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ኃጢያት ገባ። ከዚያም በኋላ የተከተለው የአዳም ትውልድ ሁሉ በኃጢያት ስር ወደቀ።

ጌታችን ኢየሱስ ከቅድስት ድንግል ማሪያም ተወልዶ በመስቀል ላይ የሞተው በኃጢያት ምክንያት የመጣብንን የሞት ፍዳ ለመክፈል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የአለምን ኃጢያት ሁሉ ተሸክሞ በመስቀል ላይ በመዋል፣ ስጋው ተቆርሶ፣ ደሙ ፈሶ ለአለም ሁሉ የሚሆን የደህንነት ቤዛ ሆኗል። በክርቶስም መስቀል በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የለየው ኃጢያት፣ በኃጢያትም ምክንያት በሰው ላይ ነግሶ የነበረው ሞት ተነስቷል። እግዚአብሔር በባህሪው ፍጹም ጻዲቅ ፍጹምም መሃሪ በመሆኑ የክርስቶስ ሞት የኃጢያትን ቅጣት በመክፈል የእግዚአብሐርን ጽድቅ ፈጸመ። የክርስቶስ ትንሳዔ ደግሞ የእግዚአብሔርን ምህረትና የማዳን ኃይል በመግለጽ ሙታን ለነበርን ለኛ የድነት መንገድ ሆነ። ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነን በሞቱና በትንሳኤው ስንተባበር ለኃጢያት ሞተን ለጽድቅ ህያዋን እንሆናለን።

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያዘጋጀው ብቸኛው የመዳን መንገድ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ "መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና" በማለት ይመክረናል። (ሐዋ. 4፡12) ጌታ ኢየሱስም "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" በማለት ይህንኑ አረጋግጦልናል። (ዮሐ. 14፡6) መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሚል "የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።" (ሮሜ 6፡23)

ለደህንነት የሚያስፈልገውን ዋጋ ሁሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍሎልናል። ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተው በኛ ፋንታና በኛ ምትክ ነው። እኛ መሞት ሲገባን እርሱ ሞተ። በእርግጥም እግዚአብሔር ገና ኃጢያተኞች እያለን ወዶናል። ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ "ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል" ይለናል። (ሮሜ 5፡8) እግዚአብሔር ታላቅ የፍቅር ግብዣ አድኅ እየጠራን ነው። የኛ ፋንታ ይህንን መድኃኒት ወስደን ከኃጢያት በሽታ መፈወስና የዘላለምን ሕይወት መቀበል ነው። ይህንን የመዳን ግብዣ ቸል ብንል ግን እድል ፋንታችን የዘላለም ሞት ይሆናል። እግዚአብሔር ልጁን እስከ መስጠት ወዶናል። ለፍቅሩ ምላሽ መስጠት የኛ ፋንታ ነው።